**ዮም ፍሥሓ ኮነ!**
**በእንተ ፍልሰታ፡ ውስተ አርያም!**
**ለእግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም!**

*ይድረስ፦ በቅዱሱ ኪዳን፡ ለተከበርኸውና ለተወደድኸው ኪዳናዊ ወንድሜ ፈቃደ-ሥላሴ፤*

**የመጀመሪያው የመልስ ደብዳቤ መግቢያ።**

*አንተን፡ ከተከበሩትና ከተወደዱት ኪዳናውያትና ኪዳናውያን የቅዱሱ ኪዳን ቤተሰብህ ጋር፡ እኛንም፡ ኹላችንንም፡ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴነቱ፡ በያለንበት የሚጠብቀን፡ ቸሩ አምላካችን ምስጋና ይድረሰው!*

*ዐሥረኛውን መለኮታዊ ዐዋጅ በሚመለከት፡ በጥር ፳፩ ቀን፥ ፳፻፰ ዓ. ም. የጻፍህልኝ እ-ጦማርህ፡ ከነዐባሪዎቹ ደረሰኝ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።*

*ደብዳቤህ፡ በኹለንተናው፡ እንደተለመደው፡ በመንፈስ ቅዱስ የዕውቀትና የእውነት ቃላት የተመላ በመኾኑ፡ ፈጣሪያችንን፡ በሓሤት አመሰገንሁት፤ ለአንተም፡ ከአድናቆት ጋር፡ የበኵሌን ምርቃት አበረከትሁልህ።*

*መልእክትህ፡ የመንፈስ ቅዱስ ስለኾነ፡ እየራሳቸው፡ የኢትዮጵያ ልጆች ብቻ ሳይኾኑ፡ ሌሎቹም ወገኖች ኹሉ ይመለከቱት ዘንድ፥ ተመልክተውም፡ በመንፈስ ቅዱስ የዕውቀትና የእውነት በረከት እንዲጐለምሱ ሊያደርጉ ይቻላቸው ዘንድ፡ በብዙኃኑ የጎዋ መገናኛዎቻችን ላይ አሥፍረው፡ ለይፋ ምንባብ እንዲያበቁት፡ ቅጂውን፡ ከዚህ እ-ጦማሬ ጋር በማያያዝ፡ ለአገልግሎት ባልደረቦቼ፥ እንዲሁም፡ ለኪዳናውያትና ለኪዳናውያን እኅቶቻችንና ወንድሞቻችን ጭምር ያስተላለፍሁት መኾኔን ስገልጽልህ፡ በደስታ ስሜት ኾኜ ነው።*

**የኹለተኛው የመልስ ደብዳቤዬ መግቢያ።**

*በሰላማችን በኢየሱስ መሲሕ፡ በያለንበት፡ ከእነቤተሰቦቻችን፡ በሰላም እንደምንገኝ አምናለሁ።*

*"ባለፈው በላክሁት ደብዳቤ ላይ፡ ከዐሥረኛዉ ዐዋጅ መልእክት ላይ ስገለብጥ፡ ባለማወቅ ያጎደልኩት ጽሑፍ ስላለ፥ እንዲሁም አንድ ተጨማሪ ጥያቄ ስላከልኩበት፡ በጥር ሃያ አንድ ቀን የተጻፈው ደብዳቤዬ፡ በዚህ እንዲተካልኝ በትሕትና እጠይቃለሁ!" ስትል፡ የላክኸው እ-ጦማርህ፡ ከነዐባሪዎቹ ደረሰኝ፤ እግዚአብሔር ይስጥልኝ።*

*ይህን ኹለተኛውን ተከታይ መልእክትህን ያገኘሁትና ያነበብሁት፡ ለመጀመሪያው ተመሳሳይ ደብዳቤህ፡ ያዘጋጀሁትን መልስ፡ በጎዋው የእ-ጦማር መስመራችን እንዳስተላለፍሁልህ፡ ወዲያው ነበር። እስካኹን ደርሶህ ሳትመለከተው እንዳልቀረህ እገምታለሁ።*

በዚህ በአኹኑ ደብዳቤህ ያቀረብኸው መጠይቃዊ አስተያየት፡ በቀደመው እ-ጦማሬ: የተሰጠውን መልስ የሚለውጠው አይደለም፤ እንዲያውም፡ በበለጠ የሚያጠናክር፡ ተጨማሪ የእግዚአብሔር የምስክር ቃልን እንዲያካትት የተደረገበትን፡ የተሟላ መልሴን፡ ከዚህ ጋር አያይዤ እንድልክልህ፡ ጠቃሚ ምክንያት ኾኖኛልና፡ ተመልከተው! ተጨማሪው፡ ይህ የእግዚአብሔር የምስክርነት ቃል፡ በቀይ ቀለም፥ አንተም፡ በ፪ኛው ደብዳቤህ ውስጥ ያከልከው ጽሑፍህ፡ በብጫ ተቀልመው ታያቸዋለህ። ኹሉንም፡ ካየሃቸው በኋላ፡ ወደጥቁረታቸው ልትመልሳቸው ይቻላል።

አዲሱን፡ ኹለተኛ ደብዳቤህንና ለዚሁ ደብዳቤህ፡ በእኔ በኩል የሰጠሁህን፡ ይህን የተሟላ መልስ፡ እንዳለፈው ጊዜ ኹሉ፡ የክህነት ባልደረቦቼ፡ ለእየራሳቸው ተመልክተውት፡ በቀደመው ፋንታ፡ ይህንኛውን ተክተው፡ ለይፋ ምንባብ ጭምር በማብቃት፡ በብዙኃኑ የጎዋ መገናኛዎቻችን ላይ እንዲያሠፍሩት፥ የቀሩት ኪዳናውያንና ኪዳናውያት ተባባሪዎቻችንም፡ ለእየራሳቸው ይመለከቱት ዘንድ፡ የተለዋወጥናቸውን ደብዳቤዎች ቅጂ፡ እንደአስፈላጊነቱ፡ በኹለቱም የሰነድ ቅጻቸው ያስተላለፍሁላቸው መኾኔን እንድታውቀው ይኹን!

## "ጌታዬ!" ስለሚለው ቃል።

ከዚሁ መልእክትህ ጋር ዐብሮ ሊነበብ የሚያስፈልገውን፥ ላቀረብክልኝ፡ ለተገቢው ጥያቄህ፡ መልስ የኾነውን አጭር ሓተታ፡ በዚሁ፡ እ-ጦማሬ ውስጥ እንደሚከተለው አክዬ ልኬልሃሁ።

ለደብዳቤህ፡ መነሻ ባደረግኸው፡ በ፲ኛው መለኮታዊ ዐዋጅ ውስጥ፡ እግዚአብሔር አብን፡ "ጌታዬ!" እያለች የምትጠራው ማን እንደኾነች፡ በትክክል ለይቶ ማወቁ፥ ይህስ እንዴት ሊኾን እንደቻለ መገንዘቡ፡ ለኹላችንም፡ እጅግ አስፈላጊ ነው። ጥያቄህ፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ ሲታይ፡ በቀጥታ፡ በመንፈስ ቅዱስ አነሣሽነት፡ ታስቦ የቀረበ መኾኑ፡ በገሃድ ይታወቃል።

ይህን ምሥጢራዊ እውነታ፡ እንዲህ በሚል ቃል እገልጸዋለሁ፡- እግዚአብሔር እም የተዋሓደቻትና ከዚህ የተነሣ፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕን፡ በእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስ ግብር፡ ከእግዚአብሔር አብ፡ በሰውነት የወለደችው፡ **ሰብኣዊቷ ድንግል ማርያም** መኾኗ፡ በቅድሚያ እንዳይዘነጋ ያስፈልጋል። እርሷ፡ ሰብኣዊቷ ድንግል ማርያምም፡ የተፈጥሮ ሰውነቷን፡ በንጽሕናዋና በቅድስናዋ ፍጹምነት፡ ለእግዚአብሔራዊው የአካል ምንነትና የባሕርይ ማንነት አብቅታ በመገኘቷ፡ ያ፡ ኹለንተናዊው መለኮታዊ ተዋሕዶ፡ በእርሷ ላይ ሊፈጸም ችሏል።

ስለዚህ፤ እግዚአብሔር እም፡ እግዚአብሔር አብን፡ "ጌታዬ!" ብላ መጥራት የጀመረችው፡ የድንግል ማርያምን ቅድስት ሰውነት፡ ከተዋሓደችባት አፍታ አንሥቶ ነው፤ "ጌታዬ!" የምትለውም፡ ቀዳሚ በኾነው፡ በእግዚአብሔር እም፡ መለኮታዊ አካሏና ባሕርይዋ በተዋሓደችው፡ በቅድስት ድንግል ማርያም ሰውነት እንጂ፡ በመለኮታዊ አካሏና ባሕርይዋ ብቻ አይደለም።

ከሥጋዌ በፊት፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር እም፡ በመለኮትነቷ፡ የድንግል ማርያምን ሰውነት፡ ከመዋሓዱ አስቀድሞ፡ በእግዚአብሔር አብና በእግዚአብሔር እም መካከል፡ ላለው ንግግር፡ ይህን የመሰለው ቃል አስፈላጊ ባለመኾኑ፡ በዚያን ጊዜ፡ ህልውና እንዳልነበረው፡ እሙን ነው። ምክንያቱ፡ አንተም እንዳስረዳኽው፡ አባትም [እግዚአብሔር አብም]፥ እናትም [እግዚአብሔር እምም]፥ ልጅም [እግዚአብሔር ወልድም]፥ ሠራፂው መንፈሳቸውም [እግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም]፡ ኹሉም፡ አንድ እና እኩል ስለኾኑ ነው።

ኋላ ግን፡ ራሱን፡ በራሱ ያጠፋውን፣ ከእርሱ የተነሣም፡ ራሱን ብቻ ሳይኾን፡ መላውን ፍጥረታቸውን ያማሰነባቸውን ሰብአዊውን ፍጡራቸውን ለማዳን ሲሉ፡ እኒሁ እናትና ልጅ፡ በአባትና በመንፈስ ቅዱሳቸው የስምምነት ፈቃድ፡ ያንኑ የጠፋና የማሰነ ሰውነት ለብሰው፡ እርሱኑ [ሰብአዊውን ፍጡራቸውን] እና መላ ፍጥረታቸውን በመቤዠት ለማዳን፡ ሰው በኾኑ ጊዜ፡ "ጌታዬ!" የሚለውና እርሱን የመሰሉ አዳዲስ ቃሎች እንዲፈጠሩ አስፈላጊ ኾነ።

እርሷ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ እርሱን፡ እግዚአብሔር አብን፡ "ጌታዬ!" ብላ በምትጠራበት ጊዜ እኮ፡ እርሱ፡ እግዚአብሔር አብ ደግሞ፡ ከእርሷ ብቅዓትና ትሕትና የተነሣ፥ ለእርሷ ባለው ፍጹም ፍቅርና አክብሮትም የተነሣ፥ ለታማኞቹ የቅዱሱ ኪዳን ልጆቻቸው ኢትዮጵያውያውያንና ኢትዮጵያውያትም አብነት ለመኾንም፡ እርሷን፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፡ "እመቤቴ!" ብሎ፡ እንደሚጠራት የታወቀና የታመነ ነው።

ይህ እውነታ፡ የእግዚአብሔር በኾኑት፡ በኢትዮጵያ ልጆች ዘንድ፡ ምንጊዜም፡ የሚዘነጋ አይደለም። እኒሁ ኪዳናውያትና ኪዳናውያን ልጆቻቸው፡ ይህንኑ መለኮታዊ አብነት፡ በሥርዓት ተከትለው፡ በተቀደሰው የጋብቻና የትዳር ሕይወታቸው፡ እነሆ! ለዝንተ ዓለም፡ በባልና ሚስትነታቸው፡ ሲሠሩበት ኖረዋል፤ ዛሬም፡ እየኖሩበት ይገኛሉ፤ ወደፊትም፡ ይኖሩበታል።

የፀረ-እግዚአብሔሩና የፀረ-ማርያሙ የክፋት ኃይል አገልጋዮች የኾኑት አይሁዳውያንና ግብዞቹ፡ የስም ክርስቲያኖች፡ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ቅድስት እናቱን፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን፡ "'አንቺ ሴት! ሴትዮ!' እያለ ነው ይጠራት የነበረው!" ብለው፡ እጅግ ከባድ በኾነና ሊሰረይ በማይቻለው የድፍረት ኃጢአታቸው፡ አዲስ ኪዳን በተባለው መጽሓፋቸው ውስጥ፡ አሥፍረውት እንዲገኝ ያደረጉትን፡ ይህንኑ ሰይጣናዊ የተንኰል ሥራቸውን፡ ይኽው፡ የኢትዮጵያ ልጆች፡ ሕያው በጎ ምግባር፡ የሚያጋልጥና የሚያፈራርስ መኾኑ እርግጥ ነው።

ይህን እውነታ፡ ማለትም፡ እግዚአብሔር እም፡ ቅድስት ድንግል ማርያም፡ እግዚአብሔር አብን፡ በዚህ፡ "ጌታዬ!" በሚለው፡ የአክብሮት ቃል እንድትጠራው ያደረጋትን መለኮታዊ ምክንያት፡ በቀላሉ ለማስረዳት፥ ለመረዳትም የሚያስችል፡ ፍጹም የኾነ፡ በቂ ማስረጃ አለ። ይኽውም፡ የታወቀው የልጁ የወዳጁ፡ የራሱ የእግዚአብሔር ወልድ የኢየሱስ መሲሕ ምንነትና ማንነት ነው።

ማስረጃነቱም፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ፡ በቀደመው መለኮታዊ ህልውናው፡ ከእግዚአብሔር አብ እና ከእግዚአብሔር እም፥ ከእግዚአብሔር መንፈስ ቅዱስም ጋር፡ በዕሪና፡ ማለትም፡ በአንድነትና በሦስትነት፡ የእኩልነት አኗኗሩ እያለ፡ ኋላ፡ በዘመነ ሥጋዌው፡ ሰው በኾነበት፡ በዚያ፡ የመለኮት ማንነቱና የትስብእት ምንነቱ፡ "ዘርእየ ኪያየ፡ ርእዮ ለአብ! ...በከመ አነ፡ በአብ፤ ወአብ፡ ብየ!"

ማለትም፡ እኔን ያየ፡ አብን አይቷል! ...እኔ፡ በአብ እንዳለሁ፥ አብም፡ በእኔ አለ!" በሚለው ቃሉ ይረጋገጣል።

ሰላማችን፡ እግዚአብሔር ወልድ፡ ኢየሱስ መሲሕ፡ በዚያው፡ በዘመነ ሥጋዌው የትስብእት ህልውናው፡ እንዲያ ለሓዋርያቱ ተገልጦላቸው እያለ፡-

-ከጥቂት ሰዓቶች በኋላ፡ ተለይቷቸው የሚኼድ መኾኑን፡ ከአንደበቱ ሲሰሙ፡ በኀዘንና በትካዜ የተዋጡትን ደቀ መዛሙርቱን፡ ለማጽናናት ባሰማቸው ቃሉ፡ "ሶበሰ ታፈቅሩኒ፡ እምተፈሣሕክሙ በሓዊሮትየ፡ ኀበ አብ፤ እስመ ውእቱ አብ፡ የዐብየኒ።"

ማለትም፡ "የምትወዱኝስ ብትኾኑ፡ ከእኔ አብ ይበልጣልና፡ ወደአብ በመኼዴ፡ ደስ ባላችሁ ነበር።" አላቸው፤

-ስለዳግመኛ አመጣጡም ሲነግራቸው፡ "ወበእንተሰ ይእቲ ዕለት፣ ወኪያሃ ሰዓት፡ አልቦ ዘየአምራ፣ ኢ መላእክተ ሰማይ፥ ወኢ ወልድ፣ ዘእንበለ አብ ባሕቲቱ።"

ማለትም፡ "ስለዚያች ቀንና ስለዚያች ሰዓት ግን፡ ከአባት ብቻ በቀር፡ የሰማይ መላእክትም ቢኾኑ፥ ወልድ (ልጅ)ም ቢኾን፡ የሚያውቅ የለም!" አለ፤

-ከትንሣኤው በኋላ፡ ለማርያም መግደላዊት፡ "ሑሪ ኀበ አኀውየ! ወበሊዮሙ! 'አዐርግ ኀበ አቡየ፥ ወአቡክሙ! ኀበ አምላኪየ፥ ወአምላክክሙ!"

ማለትም፡ "ወደወንድሞቼ ኼደሽ፡ ‹'እኔ፡ ወደአባቴና ወደአባታችሁ፥ ወደአምላኬና ወደአምላካችሁም ዐርጋለሁ!' ብለሽ ንገሪያቸው!› አላት" የሚሉ ቃላትን በመሰሉ ንግግሮች ያሰማቸው መልእክቶች፡ የሰውነትን ሥጋ፡ በመልበሱ ምክንያት፡ ለተነሣንበት ጥያቄ፡ መልስ የኾነውን፡ ያን እውነታ ለማመልከት የተነገሩ እውነቶች መኾናቸው፡ በእርግጥ የታወቀ ይኾናል።

እንዲሁም፡ "ወዘአሕጸጸሰ ሕቀ እመላእክቲሁ፤ ናሁ ንሬኢ፡ ከመ ኢየሱስ ውእቱ፡ በእንተ ሕማመ ሞቱ፡ ክብረ፥ ወስብሓተ፡ ዘተከለለ፤ እስመ በጸጋ እግዚአብሔር፡ በእንተ ኵሉ፡ ይጥዕሞ፡ ለሞት።"

ማለትም፡ "ነገር ግን፡ በእግዚአብሔር ጸጋ፡ ስለሰው ኹሉ፡ ሞትን ይቀምስ ዘንድ፡ ከመላእክት ይልቅ፡ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን፡ ከሞት መከራ የተነሣ፡ እነሆ፡ የክብርና የምስጋና ዘውድን ተቀዳጅቶ እናየዋለን።"

ከዚህም ጋር፡ "ኵልክሙ ፍጹማን! ዘንተ ሐልዩ! ለነሂ፤ ዘከመ ገብረ ለነ፡ ኢየሱስ ክርስቶስ። ዘውእቱ አርአያሁ ለእግዚአብሔር፡ አኮ ሀይዶ፡ ዘኮነ እግዚአብሔር። አላ አትሒቶ ርእሶ፣ ነሥአ አርአያ ገብር፤ ወተመሰለ፡ ከመ ብእሲ። ወኮነ፡ ከመ ሰብእ፤ ወሰምዐ፥ ወተአዘዘ፡ እስከ በጽሐ ለሞት፤ ወሞቱሂ፡ ዘበመስቀል።"

ማለትም፡ "ፍጹማን የኾናችሁ፡ ኹላችሁ! ኢየሱስ ክርስቶስ፡ ለእኛ ያደረገልን፡ ይህ አሳብ፡ በእናንተ ዘንድ ደግሞ ይኹን! እርሱ፡ በእግዚአብሔር መልክ ሲኖር ሳለ፡ እግዚአብሔርነቱን ለራሱ አልቀማም፤ ራሱን አዋርዶና የባሪያን መልክ ይዞ፥ በሰው ምሳሌ ተገለጠ እንጂ። በምስሉም፡ እንደሰው ኾኖ፡ መለኮታዊ ፈቃዱን ሰምቶ፡ ትእዛዙን ለመፈጸም፡ ራሱን፡ ለሞት አሳልፎ፤ ይኸውም፡ ለመስቀል ሞት እንኳ እስከመስጠት የበቃ ኾነ!" ተብለው የተጻፉት የቅዱሳት መጻሕፍት ቃላትም፡ ይህንኑ እውነታ ያጠናክራሉ።

ከኹሉም ይልቅ፡ ለዚህ መለኮታዊ እውነታ፡ ፍጹም አማናዊነት፡ መሠረትና ዓምድ የኾነ፥ ሌላ የድጋፍ ማስረጃ ሳያስፈልገው፡ በራሱ ብቻ፡ በቂ ምስክርነት ያለው፡ ራሷ፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡ በራሷ መንፈስ ቅዱሳዊ አንደበቷ የተናገረችው፡ የእውነት ቃል አለ፤ እርሱም፡ እንዲህ የሚለው ነው፦

"ታዐብዮ ነፍስየ ለእግዚአብሔር! ወትትኃሠይ መንፈስየ፡ በአምላኪየ፥ ወመድኃኒየ! እስመ ርእየ ሕማማ፡ ለአመቱ። ናሁ እምይእዜሰ፡ ያስተበፅዑኒ፡ ኵሉ ትውልድ፤ እስመ ገብረ ሊተ፥ ኃይለ ዐቢያተ።

ማለትም፡ "[የሰውነት] ነፍሴ፡ እግዚአብሔርን ታልቀዋለች! [የሰውነት] መንፈሴም፡ በአምላኬና በመድኃኒቴ፡ እጅግ ደስ ይላታል! በእኔ፡ በባሪያዪቱ ላይ የሚደርሰውን መከራ ተመልክቷልና። ከዚህ የተነሣ፡ ለእኔና በእኔ፡ ታላላቅ ድንቅ ነገሮችን ስላደረገልኝ፡ እነሆ፡ ከዛሬ ጀምሮ፡ ትውልዶች ኹሉ፡ 'የተባረክሽና የተመሰገንሽ!' ይሉኛል።"

እግዚአብሔር እም፡ ይህን የጸሎት ቃል የተናገረችው፡ በተዋሓደችው፡ በድንግል ማርያም ሰውነቷ መኾኑ፡ ለኪዳናውያትና ኪዳናውያን የኢትዮጵያ ልጆች ግልጽ ነው። መለኮታዊዉና ትስብእታዊው ልጇ ኢየሱስ መሲሕ፡ በምድር ላይ፡ በሕይወተ-ሥጋ እየተመላለሰ በሚያስተምርበት ጊዜያት ኹሉ፡ በሰውነቱ፡ ወደሰማይ አባትና እናቱ ሲጸልይ እንደኖረ ማለት ነው።

አዎን! እርሱ ልጇ ወዳጇ፡ በመጨረሻ፡ በመስቀል መከራው ላይ ሳለ፡ ነፍሱን በቤዛነት፡ ለሞት አሳልፎና ከሥጋው ለይቶ ከመስጠቱ በፊት፡ "አባ ሥረይ ሎሙ! እስመ በዘኢየአምሩ ይገብሩ!"

ማለትም፡ "አባት ሆይ! የሚያደርጉትን አያውቁምና፡ ይቅር በላቸው!" ብሎ፡ በሰውነቱ ያሰማው ጸሎት፡ በአማኞቹ መካከል፡ ዘወትር ሲዘከር ይኖራል።

አንተ ኪዳናዊ ወንድሜም፡ በደብዳቤህ ውስጥ፡ "እርሱ እግዚአብሔር፡ በሥጋ ማርያም በተገለጠ ጊዜ፡ አንድም ለእኛ አርአያ ለመኾን፥ አንድም የፍጡሩን ሥጋ መልበሱን ለማጠየቅ፡ ከእርሱ በላይ አምላክ፥ ወይንም፡ ፈጣሪ፥ ወይንም፡ እግዚአብሔር እንደሌለ፥ በመስቀሉም፡ የመድኅንነት ተግባሩን እየፈጸመ መኾኑን እያወቀ፡ እግዚአብሔር አብን፡ 'ኤሎሄ! ኤሎሄ! ኤልማስ፤ ላማ ሰበቅታኒ! ዘበትርጓሜሁ ይብል፡ አምላኪየ! አምላኪየ! ለምንት ኀደግሀኒ!'

"ማለትም፡ 'አምላኬ! አምላኬ! ስለምን ተዉኸኝ?!'" ብሎ የመጥራቱን ነገር በማዘከር፡ ያመለከትኸው ፍሬ-ነገር፡ ለዚሁ እውነታ፡ ተጨማሪ ማስረጃ ነው። (ማቴ. ፳፯፥ ፵፮። ማር. ፲፭፥ ፴፬። ሉቃ. ፪፥ ፴፬-፴፭፤ ፳፫፥ ፵፮። ዮሓ. ፲፱፥ ፳-፲፪፤ ፳፳፤ ፳፥ ፲፯። ፊል. ፪፥ ፭-፰። ዕብ. ፪፥ ፯-፱።)

"<u>ጌታዬ!</u>" ማለቷ፡ አግባብ ነው።

እንግዴህ፡ ከእነዚህ፡ ከቅዱሳቱ መጻሕፍት ምስክርነት የተነሣ፥ ማለትም፡ ልጇ ወዳጇ እግዚአብሔር ወልድ ኢየሱስ መሲሕ፡ <u>በትስብእቱ ምክንያት</u> የኾነውንና ያለውን፡ እውነተኛ ማንነቱንና ምንነቱን፡ በማያጠራጥር ኹኔታ፡ አረጋግጦ ለማሳወቅ፡ እነዚያን ቃላት፡ ከመለኮታዊው አንደበቱ አፍልቆ፡ እንዲያ፡ በግልጽ ከተናገረ፡ **እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምም፡ ልክ እንደእርሱ፡ እንደልጇ ወዳጇ ቃል፡ <u>በትስብእትነቷ [በሰብአዊነቷ] ምክንያት፡</u> እግዚአብሔር አብን፡ "<u>ጌታዬ!</u>" ብላ የመጥራቷ አግባብነት፡ "ትክክል ነው! አማናዊም ነው!" ተብሎ፡ በገሃድ ይረጋገጣል።**

**እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያም፡**
**በቅድስት ሥላሴነት ያላት ቦታ።**

በዚህ አጋጣሚ፡ መንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ የኾነችውን፡ እግዚአብሔር እም ድንግል ማርያምን በሚመለከት፡ ኹለት መለኮታውያን እውነቶችን የያዘ፡ አንድ፡ ዋና ቍም-ነገርን፡ እዚህ ላይ አንሥቼ፡ ለጊዜው፡ በመጠኑ ላብራራ እወድዳለሁ። ይኸውም፡-

፩ኛ፡ እግዚአብሔር፡ "በአንድነትና በሦስትነት ሲጠራና ሲመለክ ይኖራል!" በምንለው፡ በዚህ፡ በሥላሴ የ"አንድነትና የሦስትነት ምሥጢር" ውስጥ፡ **እግዚአብሔር እም፡** አራተኛ አካልና ባሕርይ መስላ እንዳትታይ የሚያደርገው፡ መለኮታዊ እውነታ ነው፤ እርሱም፡ እንዲህ በሚል፡ ምጥን ቃል ሊገለጥ ይቻላል፡-

ከፍጥረተ ዓለም በፊት በነበረው፡ በቀደመው፡ በመለኮታዊው ምሥጢረ ጋብቻ ኾነ፥ ኋላ፡ በፍጥረተ ዓለም፡ በአዳምና ሔዋን ጊዜ፡ በዚያው በመለኮታዊው አርአያ በገዘፈው፡ በሰውኛው የጋብቻ ሥርዓት፡ ባልና ሚስት፡ **"ወይከውኑ ክልኤሆሙ፡ አሓደ ሥጋ። እንከሰኬ፡ ኢኮኑ ክልኤተ፤ አላ፡ አሓዱ ሥጋ እሙንቱ። ዘእግዚአብሔር አስተፃመረ፡ ሰብእ ኢይፍልጥ!"**

ማለትም፡ "ኹለቱም፡ አንድ ሥጋ ይኾናሉ፤ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ፣ ወደፊት ኹለት አይደሉም፤ እግዚአብሔር፡ እንዲህ፡ አንድ ያደረገውን፡ እንግዴህ፡ ሰው፡ አይለየው!" በሚለው፡ ለሰው በተነገረው አምላካዊ ቃልና በተሰጠው አምላካዊ መመሪያ መሠረት፡ ቀዳሚው፡ የእግዚአብሔር አብ እና የእግዚአብሔር እም አንድነት፡ በዚህ መልኩና ይዘቱ የጸና መኾኑን በማጠየቅ፡ <u>እግዚአብሔር አብ እና እግዚአብሔር እም፡ ምንጊዜም የማይለያዩ፥ በፍጹም የአንድነት ህልውናቸውም፡ በአንድነት የሚጠሩና በአንድነት የሚመለኩ፥ በአንድነት የሚሠሩና በአንድነት የሚመሰገኑ፡ ፍጹም አንድ መኾናቸውን የሚያረጋግጠው እውነታ ነው።</u>

ቅድስት ሥላሴ፡ "ቅዱስ! ቅዱስ! ቅዱስ!" ተብለው፡ በአንድነት በሚጠሩበትና በአንድነት በሚገኙበት፥ በአንድነት በሚመለኩበትና በአንድነት በሚመሰገኑበት፥ በአንድነት በሚሠሩበትም፡ በኢትዮጵያ፡ የእግዚአብሔር መንግሥት ዘንድ፡ በሥርዓተ ጸሎታችን ጊዜ፡ በተግባር ላይ ውሎ፡ ሲካኼድና ሲፈጸም እንደሚታየው ማለት ነው።

ይህም እውነታ፡ ሥላሴ፡ በሦስት ሰዎች ተመስለው፡ በቤተ አብርሃም፡ በእንግድነት በተገኙ ጊዜ ተከሥቷል፤ ይኸውም፡ "ቦኑ ነገር፡ ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር? በዝንቱ ጊዜ፡ ሶበ ገባእኩ ኀቤከ፡ በሳብዕታ፡ ትረክብ ሳራ ወልደ!" ማለትም፡ "በውኑ፡ ለእግዚአብሔር የሚሳነው ነገር አለን? እንደዛሬው ጊዜ፡ ወደአንተ በምመለስበት፡ በመጪው ዓመት፡ በሰባተኛው ወር፡ ሳራ፡ ወንድ ልጅን ታገኛለች!" የሚለውን፡ አምላካዊ የተስፋ ቃል፡ በዚሁ፡ በእግዚአብሔር አብወእም አንድነቷ የተናገረችው፡ እግዚአብሔር እም በመኾኗ ነው።

፪ኛ፡ በግእዙ ቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ፡ የመጀመሪያው የኾነው መጽሓፍ፡ አማናዊው ስያሜውና ትክክለኛ አርእስቱ፡ "ኦሪት ዘልደት" የሚል ሲኾን፡ በአጼ ኃይለ-ሥላሴ ዘመን፡ በባዕዳኑ አብያተ ክርስቲያናት አነሣሽነትና መሪነት፥ ተፅዕኖና ባለቤትነት፡ የተተረጐመው፡ የዚሁ መጽሓፍ ስያሜ፡ በስሕተት፡ "ኦሪት ዘፍጥረት" ተብሎ፡ ይኸው በዚሁ ስሑት ርእሱ፡ ቀጥሎበት ይገኛል።

በግእዙ ቅዱሳት መጻሕፍት፡ ይኸው መጽሓፍ፡ "ኦሪት ዘልደት" የተባለው፡ እንዲያው፡ ያለበቂ ምክንያት፡ በከንቱ አይደለም። ልደት ኹሉ፡ ያለእግዚአብሔር እም፡ በእግዚአብሔር አብ ብቻ ሊኾን እንደማይቻል፥ ፍጥረታትም ኹሉ፡ ሰው ጭምር፡ በነፍስም፥ በሥጋም፥ በመንፈስም፡ በእግዚአብሔር በመፈጠር ብቻ ሳይኾን፡ ከእግዚአብሔር በመወለድ ጭምር የተገኘ መኾኑን ለማጠየቅ መኾኑን፡ የኢትዮጵያ ልጆች፥ ሌላውም ሰብአዊ ፍጡር ኹሉ፡ ሊያውቀውና ሊገነዘበው ይገባል። (ዘፍጥ.፪፥ ፳፩፤ ፲፰፥ ፲፬። ማቴ. ፲፱፥ ፬-፮።)

\+ + +